የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ የኢፌዲሪ መንግስት የቀየሳቸውን የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዕቅዶች ከግብ ለማድረስና በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል የ5 ዓመት ስትራቴጂ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ዕቅድ ነድፎ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል።

ኤጀንሲው በ2002 የበጀት ዓመት የሚከተሉትን አበይት ተግባራት አከናውኗል።

- በሚኒስቴር መ/ቤት ደረጃ የተጠናውን የመሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ (BPR) ጥናት አጠናቅቆ የሙከራ ትግበራ በማካሄድ በቼክ ሊስት የመከታተልና ለBPR ተግባራት የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለጻ የመስጠት ሥራ አከናውኗል፣
- ከክልልና ከማዕከል ለተውጣጡ ሠራተኞች በቤተመዛግብት፣ በቤተመጻሕፍትና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስልጠና እንዲያገኙ አድርጓል፣
- የስልጠና ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጥቷል፣
- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የማስፋፋትና የመረጃ ሥርዓት ዝርጋታ ፕሮግራሞችን በማከናወን የኤጀንሲውን አሠራር ዘመናዊ ለማድረግ የኔትወርክ ዝርጋታ ላይ ክትትል የማድረግ ሥራ ተከናውኗል፣
- የተቋሙን የመረጃ ሃብቶች ደህንነት ለማስጠበቅ በኤሌክትሮኒክስ ፎርማት ያሉ መረጃዎችን ባክአፕ የማድረግ ሥራ ተከናውኗል፣
- በሳይበር ሶፍትዌር የተዘጋጀውን ሥራ ላይ እንዲውል የመከታተል ሥራ አከናውኗል።
- የተቋሙን ሪከርዶች የመጠበቅ፣ ከአደጋ የመከላከልና የመጠገን ሥራ ተሠርቷል፣
- የበጀት ዓመቱን የዕቅድ አፈጻጸም በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ፣ በመንፈቅና በ9 ወራትና በበጀት ዓመቱ ማጠቃለያ ላይ በሪፖርት በማቅረብ የማስገምገም ሥራ ተሠርቷል፣
- የነባሩን ህንፃ ዕድሳት በማጠናቀቅ ለአገልግሎት የማብቃት ሥራ ተሠርቷል፣
- በBPR ጥናት መሠረት በየወሩ የተቀመጡ ግቦችን በመገምገም የማስተካከያ ሥራ ተከናውኗል፣
- ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ተቋሙ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሙያ የተደገፈ የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፣
- የመዛግብት ክምችቶችን የመረጃ አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት 98 ፐርሰንት ተከናውኗል፣
- በአፈጻጸም ወቅት በአሠራር ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማስወገድ የፕሪዘርቬሽን ፖሊሲ የማጠናቀቅ ሥራ ተሠርቷል፣
- በቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ሙያዎች ላይ የተሠማሩ ሠራተኞችን ክህሎት ለማሳደግ የሥራ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፣

- ተገልጋዮች ባሉበት የሙያ ክህሎት ለማሻሻል እንዲችሉ በድረ-ገጽ ስልጠና ለማስጠት የE-training አስፈላጊ የቅድመ ሁኔታዎች ጥናት ተካሂዷል፣
- የNIRLMS software በተመረጡ መ/ቤቶች ሥራ ላይ እንዲውል ከኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ጋር በመተባበር የክትትል ሥራ ተሠርቷል።
- በአዋጅ መብት መሠረት ከ2 አመንጪ መ/ቤቶች ሪከርዶችንና መዛግብትን በማዛወር ርክክብ የመፈፀም ሥራ ተከናውኗል፣
- በመገናኛ ብዙሀንና መረጃ ነፃነት አዋጅ መሠረት ከ4 መቶ ያላነሱ ጋዜጦች ተሰብስበዋል
- 2496 መጽሐፍ ቅዱስ ከገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤት በስጦታ ተበርክተዋል
- ለ6 የሕዝብ ቤተመጻሕፍት ፣ ለ9 ክልሎችና ለ2 የከተማ የህዝብ ቤተመጻሕፍት የመረጃ ሃብቶች ተሠራጭተዋል፣
- ከ3560 በላይ የሚሆኑ የመረጃ ሃብቶች ወደ ኤሌክትሮኒክስ ላይብረሪ ማኔጅመንት ሶፍትዌር (ELM) የመጫን ሥራ ተከናውኗል፣
- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተሠሩ ቀረፀ ድምጾችና ምስሎች እንዲሁም የተለያዩ ብትን ህትመቶችን የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ ተከናውኗል፣
- ከአመንጪ መ/ቤቶች ለተዛወሩት የመዛግብት ሲረስ ኢንቬንተሪ፣ ኢንዴክስ፣ መግለጫና ጋይድ የማዘጋጀት ሥራ ተከናውኗል፣
- በቅጂ የተመዘገቡ ሪኮርዶችን ወደ ዳታ ቤዝ የማስገባት ሥራ ተከናውኗል፣
- በ6 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሪከርድ ሰርቬይ የማካሄድ ተግባር ከ70 ፐርሰንት በላይ ተከናውኗል፣
- ለሁሉም መ/ቤቶች የጋራ የሆነ የሪከርዶች የፋይል ሲሪየስ  ጥናት በማካሄድ የሥራ መመሪያ የማዘጋጀት ተግባር ተከናውኗል፣
- የመረጃ ሃብቶችን ዲጂታይዝ የማድረግ ሥራ ተከናውኗል፣
- ውጤታማ የሰው ሃይል ልማትና አጠቃቀምን በማስፈን በቴክኖሎጂ የታገዘ ከ268748 በላይ የሚሆኑ ተገልጋዮች የመጻሕፍት፣ የጋዜጦችና የመጽሔት የኢንተርኔት አክሰስ  የንባብ አገልግሎት የመስጠት ሥራ ተከናውኗል፣
- ለዓይነ ሥውራን የንባብ አገልግሎት የኢንተርኔት ቤተመጻሕፍት የንባብ አገልግሎት የመስጠት ተግባራት ተከናነዋል፣
- የISBN ቁጥር ላልወሰዱ አታሚና አሳታሚ ድርጅቶች የISBN ቁጥር ከተቋሙ እንዲወስዱ ቅስቀሳ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል፣
- ለጥንታዊ ጽሑፎች ማፈላለጊያ የማዘጋጀትና ለአገልግሎት የማብቃት ሥራ ተሠርቷል፣
- ከቀድሞው የአገር ግዛት ሚኒስቴር ከ200.000 ሺ በላይ መዛግብትን ወደ ኤጀንሲው ለማዛወር የምዝገባ ሥራ ተጠናቋል፣
- የዲጂታል ቤተመጻሕፍት አገልግሎት የመስጠት ሥራ ተከናውኗል፣
- በመረጃ ሃብቶች በመጠቀም የንባብና ምርምር ባህሉ የዳበረ ህብረተሰብ ለመፍጠር ዓላማ ተኮር የማስተዋወቅ ኘሮግራም የማካሄድ ሥራ ተሠርቷል፣
- ለመንግስትና ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመዛግብት ስብስብ ይዘትና ስብጥር ለጥናትና ምርምር ያላቸውን ፋይዳ የማስተዋወቅ ሥራ ተከናውኗል፣
- የሥርዓተ ጾታና የኤች አይ ቪ/ኤድስ ጉዳዮችን ሜይንስትሪም በማድረግ በዕቅድ አካቶ የመተግበር ተግባራት ተከናነዋል፣
- በኤችአይቪ/ኤድስና በሥርዓተ ጾታ ጉዳዮች ላይ በተሰበሰቡ መረጃዎች የንባብ አገልግሎት የመስጠት ተግባራት ተከናውነዋል፣

- የኤችአይቪ /ኤድስ ላይ ያተኮረ የአቻ ለአቻ ውይይት በሠራተኛው የማካሄድ ሥራ ተከናውኗል፣
- የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኙ የኤጀንሲው ሠራተኞች የገንዝብና ሌሎች ድጎማዎች የማድረግ ተግባራት ተከናውነዋል፣
- ሀገራዊ መረጃ ለሀገራዊ ልማት በሚል ርዕስ የፓናል ውይይት በማካሄድ የተቋሙን የመዛግብት ስብስቦች የማስተዋወቅ ሥራ ተሠርቷል፣
- በኤጀንሲው ውስጥ የሚደረጉ ልዩ ልዩ ስብሰባዎችና ዝግጅቶች በፎቶግራፍ በቪዲዮ ተቀርፀው ለጥናትና ምርምር አገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል፣
- ተቋሙ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች የማስተዋወቅ ሥራ ተሠርቷል፣
- 1000 መጽሔቶችን ፣ 500 ብሮሸሮችንና 1000የቀን መቁጠሪያና 500 እንኳን አደረሳችሁ ካርዶችን አዘጋጅቶ በማሠራጨት የተቋሙን ዓላማ ለማስተዋወቅ ተችሏል፣
- የተቋሙን መልካም ገጽታ ለመጠበቅ እንዲቻል የሚዲያሞኒተሪንግ ተግባራትን የማከናወን ሥራ ተሠርቷል፣
- በቤተመጻሕፍት የአባልነት ምዝገባ የማካሄድና በረጅም የሪፈረንስ አገልግሎት የመስጠት ተግባራት ተከናውነዋል፣
- የኢንተር ላይብረሪ አገልግሎት የመስጠት ሥራ ተከናውኗል፡፡